# Sheep Fattening Training Manual

# የበግ ማደለብ ስልጠና ማንዋል


**Bonga Agricultural Research Center**

**ቦንጋ ግብርና ምርምር ማዕከል**



**Dec, 2018**

**ታህሳስ, 2011**

# 2. የቦንጋ በግ እርባታ ፓኬጅ

## መግቢያ

ክልላችን 4,118,382 (16.14%) ከፍተኛ የበግ ክምችት በመያዝ ከአማራና ኦሮሚያ ክልል በመቀጠል በ3ኛ ደረጃ ላይ ይቀመጣል:: በተዋረድ በክልሉ ውስጥ ያሉ ዞኖች ሲታዩ ደግሞ ደቡብ ኦሞ 842,712 (20.46%) የበግ ክምችት በመያዝ 1ኛ ሲሆን፣ ጋሞ ጎፋ፣ ካፋ፣ እና ሲዳማ ዞኖች 473,753 (11.5%)፣ 449,008 (10.9%) እና 430,490 (10.45%) በቅደም ተከተል ከ2ኛ እስከ 4ኛ ደረጃ በመያዝ ከፍተኛ ደረጃ ይዘዋል (CSA, 2007):: የበግ እርባታ ባመዛኙ በገጠር በሚኖርና አነስተኛ ገቢ ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚተገበር ሲሆን በከተሞችና ከተማ ዙሪያ አካባቢ ደግሞ በጎችን በማሞከት የተሠማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች መኖራቸውም ይታወቃል:: አርቢው ማህበረሰብ በጎችን የሚያራባው ሽጦ ለቤት ውስጥ ፍጆታ የሚውሉ ቁሳቁሶችን ከማሟላት ባሻገር ለሥጋ፣ ለሌጦ፣ ለፍግ/ ማዳበሪያ እና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች ጭምር ነው:: በአንዳንድ ቆላማ አካባቢዎች ከላይ ከተዘረዘሩት ጥቅሞች ባሻገር በጎች ለወተት ምርትም ይውላሉ::

የህዝብ ብዛት መጨመር፣ የግጦሽ መሬት መቀነስ፣ የመሬት ይዞታ እያነሰ መሄድና ተያይዞ የሚመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ በመቋቋም ረገድ አነስተኛ አመንዣኪዎች ከሌሎች እንስሳት የላቀ ችሎታ አላቸው:: በተጨማሪም የአመጋገብ ባህሪያቸው፣ የሰውነት መጠናቸው ማነስና ሥራ ለመጀመር የሚጠይቀው መነሻ ካፒታል ከዳልጋ ከብቶች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆን እንዲሁም የድርቅ ወቅትን የመቋቋም ችሎታቸው ከፍተኛ መሆንና በፍጥነት መራባታቸው በአብዛኛው የኢኮኖሚ አቅሙ አነስተኛ በሆነና የምግብ ዋስትና ችግር ባለባቸው አርሶና/አርብቶ አደሮች ዘንድ ተመራጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል::

የበግ እርባታ በሁሉም የክልሉ አከባቢዎች በተለያዩ የአረባብ ዘዴዎች ወይም ስልቶች እየተተገበረ ይገኛል:: በክልሉ ከሚገኙት ዋና ዋና የበግ እርባታ ዘዴዎች፡ የደጋማ በግ እርባታ ዘዴ (Highland sheep Production system):- በሲዳማ፣ በዳውሮ፣ ጋሞጎፋ፣ ጉራጌ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ካፋ ዞኖች ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች፤ የሰብልና እንስሳት እርባታ ጥምር አመራረት ዘዴ (crop-livestock production system):- በክልሉ ማዕከላዊና ምስራቃዊ ዞኖች በዋናነት የእርሻ ስራ በሚከናወንባቸው ሥፍራዎች እና የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር የማርባት ዘዴ (Pastoral and agro-pastoral production system):- በክልሉ ቆላማና ከፊል ቆላማ በሆኑ ደቡባዊና በተወሰኑ ምዕራባዊ ዞኖች እንስሳት እርባታ በተናጠል በሚተገበርባቸው ወረዳዎች /አርብቶ አደር አካባቢ/ ናቸው::

የተለያዩ የበግ ዝርያዎች በሀገሪቱ እንደሚገኙ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን በክልላችን ከሚታወቁት ዉስጥ በዝርያነት የተመዘገበው የቦንጋ በግ ዝርያ ብቻ በመሆኑ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የሚረቡ በጎችን ዝርያ ለመለየት የዘረ-መል ጥናት ለማድረግ ዝግጅቶች ተጠናቀዋል:: የሀገረሰብ በጎችን (የቦንጋ በግ ዝርያ እና ሌሎች የበግ መንጋዎች ማለትም የዶዮገና፣ ጉመር እና አበራ (ዳራ) በጎችን) በማኅበረሰብ አሳታፊ መረጣ (community

based selection) የማሻሻል ጥናት ባለፉት ጊዜያቶች ሲከናወን የቆየ ሲሆን እስካሁን ድረስ በተሰራው ስራ አበረታች የሆነ ዉጤት ማግኘት ተችሏል::

አሁን የተገኘው አበረታች ውጤት ወደ ላቀ ደረጃ እንዳይደርስ የተለያዩ ማነቆዎች ያሉበት ሲሆን እነዚህን ማነቆዎች ከማስወገድ አንፃር ጉልህ ሚና የሚኖራቸውን የበጎች አያያዝ ሁኔታዎች ማለትም የNegative Selection practice (በተለምዶ በፍጥነት የሚያድግ አውራ በግን የጥቂ አገልግሎት ሳይሰጥና ዘር ሳይተካ ያለዕድሜው ለገበያ የመሸጥ ልምድ)፣ Inbreeding depression (ቤተ-ዘመድን እርስ በርስ በማስጠቃት ምክንያት አማካይ የምርት መጠን የመቀነስ ሁኔታን አለመረዳት)፣ የጤና አጠባበቅ፣ የአመጋገብ ሥርዓት፣ የበግ ማደሪያና መዋያ ቤት አሠራርና የመሳሰሉትን በሳይንሳዊ ዘዴ ማሻሻል ግድ ይላል::

## 2. የፓኬጁ አስፈላጊነት

ምንም እንኳን የቦንጋ በግ በሀገሪቱ ካሉ የበግ ዝርያዎች በተለያዩ መመዘኛዎች የላቀ ቢሆንም አርቢው ማህበረሰብ የተለያዩ ተመጋጋቢና የዝርያውን ምርታማነት የሚያሻሽሉ ተግባራትን ባለማከናወኑ አሁን እየተገኘ ያለው ውጤት ከዝርያው ተፈጥሮአዊ አቅም በታች ነው:: በመሆኑም ሙሉ ፓኬጅ መቅረጽና አ/አደሩ እንዲተገብረው ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው::

## 3. የፓኬጁ ዓላማዎች

- አርሶ አደሩ በተናጠልም ሆነ በጋራ/ በማኅበር የበግ እርባታ ፓኬጁን በመተግበር የበጉን ምርታማነት በማሳደግ ገቢውን እንዲያሻሽል ማድረግ እና
- ከበግ የሚገኝ ሥጋና ሌጦ እንዲሁም የቁም እንስሳት አቅርቦትና እሴት በመጨመር የውጭ ምንዛሬን ማሳደግ::

## 4. የቦንጋ በግ ስያሜ

የቦንጋ በግ ዝርያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተለይተው ከታወቁት ዘጠኝ የበግ ዝርያዎች አንዱ ሲሆን እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ "የሆሮ በግ ዝርያ" ተብሎ እራሱን የቻለ ዝርያነቱ ተሰውሮ የቆየ ሲሆን ከዚህ ጊዜ ወዲህ በተደረገዉ ጥናት ራሱን የቻለ ዝርያ ማለትም የቦንጋ በግ ዝርያ ተብሎ ተለይቶ ተመዝግቧል:: የቦንጋ በግ ስያሜ የተሰጠው የካፋ ዞን ዋና ከተማ ከሆነች ከቦንጋ ከተማ በመሆኑ የበጉም ስም ቦንጋ በግ ተብሎ ተሰይሟል:: የቦንጋ በግ በዋናነት በካፋ፣ ቤንች ማጂና ሸካ ዞኖች እንዲሁም በኮንታና የም ልዩ ወረዳዎች የሚገኝ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል፣ በአጎራባች ዞኖችና ወረዳዎችም ተስፋፍቶ ይገኛል::

### 4.1. የቦንጋ በግ ልዩ ባህርያት

- ከጥቁር ውጪ ሁሉም ዓይነት የፀጉር ቀለም ዓይነቶች ያሉት ሆኖ በአብዛኛው ቀይና ዳለቻ የፀጉር ቀለም ያለው መሆኑ፣
- በአርቢዎቹ ምርጫ ሁለቱም ጾታዎች (እንስቶቹም ይሁን አውራዎቹ) ቀንድ-አልባ መሆናቸው፣
- ረጅምና ሰብ ላት ያለው መሆኑ፣
- መንታ፣ ሶስትና አልፎ አልፎ አራት የመውለድ ብቃት መኖሩ፣
- የተወለዱ ግልገሎችን ለማሳደግ ያለው የእናትነት ባህርይ ብቃት ከፍተኛ መሆኑ፣
- ቶሎ የማደግና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለእርድ መድረስ መቻሉ፣
- በሀገሪቱ ካሉ በግ ዝርያዎች ውስጥ በግዙፍነቱ ቀዳሚ የሆነ መሆኑና
- ሥጋው ጣፋጭ መሆኑ የሚጠቀሱ ባህርያቶቹ ናቸው።

## 5. የቦንጋ በግ ዝርያን በመረጣ የማሻሻል ዘዴ

### 5.1. ስለስራው ምቹ አካባቢና ሁኔታዎችን በመለየት የእርባታ ዜዴ መቀየስ

በመጀመሪያ ደረጃ አንድን ስራ ከመስራት በፊት ስራውን የት? መቼ? ከማን ጋር? እንዴት? የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎችን መመለስና አስፈላጊውን ትንተና ማስቀመጥ ቀዳሚ ይሆናል። የቦንጋ በግ ዝርያን ለማሻሻል በተደረገው ጥናት መሰረት በካፋ ዞን አድዮ ወረዳ ቦቃ ቀበሌ ቦቃ-ሹታ መንደሮችን በመለየትና በግ አርቢውን በሰፊት በማሳተፍ ስለ በግ ዝርያ ማሻሻያ ከሚመለከታቸው መንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ሰፊ ግንዛቤ በመፍጠር እና ማህበረሰብ አቀፍ የቦንጋ በግ ዝርያን በመረጣ የማሻሻል ዘዴ /Open Nuclues Breeding Scheme/ በመቀየስ በክልል ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ አመርቂ ውጤት ለማምጣት ተችሏል።

በዚህ መሠረት በግ አርቢው እንዲሻሻል የሚፈልጋቸውን ባህርያት (preferred Traits) አርቢው እራሱ እንዲለይና ደረጃ እንዲሰጥ በማድረግ የተለዩ ባህርያትን በመረጣ ማሻሻል እንደሚቻል ትምህርት በመስጠትና ከአርቢው ጋር በጥምረት ምርምር በመስራት ሁሉንም የተለዩ ባህርያትን ለማሻሻል ተችሏል። ለአብነት ያህል የቦንጋ በግ ክብደትን ለማሻሻል በተሰራው ስራ በመጀመሪያው ትውልድ ብቻ የግልገሎችን የወሊድ ክብደት ከ2.5 ኪ.ግ ወደ 5.8 ኪ.ግ ከፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በ3 ወር እድሜያቸው እስከ 29 ኪ.ግ ክብደት የሚመዝኑ ግልገሎችን ማግኘት እንደሚቻል ለማረጋገጥ ተችሏል።

## 5.2. በግ አርቢውን በተለያዩ አደረጃጀቶች ማስተሳሰር

በግ አርቢውን በተለያዩ አደረጃጀቶች ማስተሳሰር የማህበራዊ ደረጃና የኑሮ ዘይቤን ከማሻሻል ባሻገር በአንድ አካባቢ የሚኖሩትን በግ አርቢዎች በተደራጀ መልኩ ማደራጀት ለዝርያ ማሻሻያ ስራው አስፈላጊነቱ ከሚያረቡት በጎች ውስጥ የተሻለ ታሪክ እና መረጃ ያለውን በግ በብዛት ለመምረጥ ቀጥተኛ የሆነ ድርሻ እንዳለው ለማየት ተችሏል:: በቦንጋ ግብርና ምርምር ማዕከልና አጋሮቹ በተደረገው ጥናት ማህበረሰብ አቀፍ የቦንጋ በግ ዝርያ ማሻሻል ስራ ጋር ተያይዞ የዝርያ ማሻሻል ስራን በዘላቂነት ለማረጋገጥ በክልላችንም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ የሆነ የበግ ዝርያን በመረጣ የሚያሻሽል የአርሶ አደሮች የህብረት ስራ ማህበር በካፋ ዞን ቦቃ ቀበሌ የቦቃ-ሹታ ምርጥ የቦንጋ በግ ዝርያ ማሻሻያ፣ ማራቢያ እና ማባዣ ህብረት ስራ ማህበር በማቋቋም በአጭር ጊዜ ወስጥ አመርቂ ውጤት ለማስመዝገብ ተችሏል::

ምንም አይነት የዝርያ ማሻሻያና የአረባብ ዘዴ ተሻሽሎ ምርትና ምርታማነት ቢጨምርም አርቢው ተገቢውን ገቢ ካላገኘ ልፋቱ ከንቱ ሆኖ ነው የሚቀረው:: ስለዚህ ምርታማነትን ከማሳደግ ሥራ ጎን ለጎን የአርቢውን የነፍስ ወከፍ ገቢ ማሳደግ የምርምሩ የመጨረሻ ግብ ነው:: ከላይ እንደተጠቀሰው የአርቢዎችን በህብረት ስራ ማህበር በማደራጀት ዝርያን እንዲያሻሽሉ፣ እንዲያራቡ፣ እንዲጠብቁና እንዲያባዙ ደግሞም ከተሻሻለው ዘር የምርጥ ምርጦችን እንዲያስቀሩና ቀሪዎችን ወደሌላ አካባቢ በሚመጥን ዋጋ የመሸጥና የመደራደር አቅማቸውን በማሳደግና በመሀል ላይ ያለውን የደላላ ቅብብሎሽ ሰንሰለት በመቁረጥ በቀጥታ ከገዥው ጋር በማገናኘት በአጭር ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ1,425 በላይ የተሻሻሉ አውራዎችን እንዲያሰራጩ በማስቻል 5,474,767 ብር እንዲያገኙ ተደርጓል:: ከዚህም በተጨማሪ የአርቢዎች ማህበር አባል በግ አርቢ አርሶ አደር ለችግሩ ሲል ያለፍላጎቱ በጎችን በየገበያው ከመሸጥ ወጥቶ ማህበሩ በሚያመቻቸው ጊዜያዊ ብድር አማካይነት አጣዳፊ ችግሩን እየተወጣ በጉን አሳድጎ አቆይቶ ዝርያውን ከተካ በኋላ በእርጋታ በተሻለ ዋጋ ማህበሩ እንዲሸጥ በማድረግና የሚገኘውን ትርፍ ደግሞ ለአባላቱ እንዲከፋፈል በማስቻል ማኅበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ አርቢውን በማደራጀት ቀጣይና ዘለቄታ ያለው የዝርያ ማሻሻያ ስራ መስራት እንደሚቻል በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል::

ይህ ብቻ ሳይሆን ይህንን መልካም ተሞክሮ ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዲሰፋ በማድረግ ያልተቋረጠ ስኬት እየተመዘገበ ሲሆን ሁሉም አካባቢዎች ይህን አይነት የዝርያ ማሻሻያ ስልት ቢጠቀሙ በአጭር ጊዜ ውስጥ የህገረሰብ በጎች ዝርያን በማሻሻል ምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ የሀገር ውስጥና የውጭ ምንዛሬ በቀላሉ ማሳደግ እንደሚቻል የተገኙ ውጤቶች ማሳያ ናቸው::

## 5.3. የእርባታ በጎችን መለየት

የዝርያ ማሻሻያ ሥራ ከመጀመር በፊት በተመረጠ አካባቢ /Community/ በዝርያ ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ፍቃደኛ የሆኑ አርሶ አደሮችን ተገቢውን ግንዛቤ በማስጨበጥ ለእርባታ የሚሆኑ በጎችን መለየት ያስፈልጋል:: በዚሁ መሠረት ፈቃደኛ አርሶ አደሮችን ምርጥ የበግ ዝርያ ማራቢያ፣ ማሻሻያና ማባዣ ህብረት

ሥራ ማህበር እንዲያደራጁ ከተደረገ በኋላ የሁሉም አርቢዎች የሚፈልጉትን ጠቃሚ ባህርያት (ፈጣን እድገት፣ መንታ መውለድ፣ የአካባቢውን አየር ንብረት ለውጥና በሽታን መቋቋም፣ የእናትነት ባህርይ ወዘተ...) በራሳቸው በአርቢዎች ከተለዩ በኋላ፣ የሁሉም አባል አርሶ አደሮች በጎች አስፈላጊ የሆነ መረጃ (የእድሜና የሰውነት ክብደት) ከተወሰደ በኃላ ጥሩ መውለድ የሚችሉ (ያላረጁና በምንም ምክንያት መውለድ ያላቆሙ) እናቶች ይለያሉ:: በተጨማሪም ለመጀመሪያ የአባትነት አቋምና መስፈርት የሚያሟላ አውራ ከተለዩት በጎች በመለየት 1 አውራ 25-30 እናቶችን እንዲያጠቃ በማድረግ ለዝርያ ማሻሻያ ስራ መነሻ የሚሆኑ በጎችን በመለየትና የማይጠቅሙትን በማኮላሸት፣ ለተለዩ በጎች መለያ (የጆሮ ቁጥር) በመስጠት የመረጣ ስራው ይጀመራል:: እናቶችና አውራዎች ከተለዩ በኃላ በተከታታይ ከእነዚህ የሚወለዱ ግልገሎች መረጃ እንደተወለዱ በዕለቱ፣ በተወለዱ በሶስተኛ፣ በስድስተኛና አስራ ሁለተኛ ወር የሰውነት ክብደትና ሌሎችን አርቢው የሚፈልጋቸውን መረጃዎች (ቁመና፣ መልክ፣ ቀንድ መኖር አለመኖር ወዘተ...) መሰብሰብ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ ስራ ዋናው አላማ ካሉት መንጋዎች ለወደፊት ጥሩ እናትነትና አባትነት ባህርያት ያላቸውን በጎች በመምረጥ የዝርያ ማሻሻያ ስራው ዘለቄታ ያለው እንዲሆን ማስቻል ስለሆነ እነዚህን ማግኘት የሚቻለው ደግሞ መረጃን መሠረት በማድረግ ስለሆነ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች መረጃዎችን መለየትና መመዝገብ ቀዳሚና የመረጣ ስራው ዋና መሳሪያ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል::

## 5.4. የመረጣ ሥራ መጀመር

የአንድ እንስሳ ዝርያ ሲነሳ ቀደም ብሎ በአእምሮአችን የሚመጣው ጉዳይ የእናትና አባት ጉዳይ ነው:: በበግ እርባታ ውስጥ የተለያዩ አርቢዎች ለጥሩ እናትነትና ለጥሩ አባትነት መለያነት የሚጠቀሙአቸው ባህርያት የተለያዩ ሲሆኑ እነዚህን የአርሶ አደሮች የመረጣ መስፈርት ባህርያት በመጠቀም ጥሩ እናትና አውራ በጎችን በመምረጥና እነዚህኑ የተመረጡ እናቶች በተመረጡት ኮርማዎች ብቻ በማስጠቃት /በማዳቀል/ ጥሩና ምርታማ ግልገሎችን ማግኘት እንደሚቻል በተደረገው ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል:: አንዲት እናት /ቄብ/ በግ ምርጥ ግልገል መውለድ የምትችለው የምታድርበት ቤትና የምታገኘው መኖ ምቹና የተመጣጠነ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እራሷ እና የሚያጠቃት አውራ ምርጥ ሲሆኑ ነው:: ይህም ባህርያቶቹ በውርስ የሚተላለፉ ስለሆነ ነው:: እንደ ቦንጋ በግ አርቢ የመረጣ ስራ ከመጀመሩ በፊት አርቢው ለአጣዳፊ የገንዘብ ችግር ቅርብ ጊዜ ጡት የጣሉ ጠቦቶችንና ለድቀላ ያልደረሱ እናት ሊሆኑ የሚችሉ ሴቶችንም ጭምር ስለሚሸጡ ለቀጣይ ዝርያ አገልግሎት የሚውሉ አውራዎችና እናቶችን በሚፈለገው ባህርያት ማግኘት ትልቅ ፈተና ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አርሶ አደሩ ጥሩ ኮርማ መርጦ እያሳደገ ስላልሆነ በጎቹን የሚያስጠቃው ጥሩ የኮርማነት ባህርይ (Libido) በሌላቸው ወይም መልካቸው ጥሩ ስላልሆነ በገበያ ዋጋ ባለማውጣታቸው አሊያም ቶሎ ባለማደጋቸው ትንሽ ቆይተው እንዲኮላሹ በሚጠበቅባቸው አውራዎች መሆኑ የአርሶ አደር አሳታፊ ውይይት በማድረግ ለመለየት ተችሏል:: በዚህም ምክንያት ከአንድ ወሊድ ወደ ሌላ ውሊድ ያለው ጊዜ መርዘም፣

አንዲት እናት በግ በሕይወት ዘመኗ የምትወልደው የግልገል ቁጥር አነስተኛ መሆንና በዚህም ምክንያት የአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት መቀነስ ዋና ዋና ችግሮች መሆናቸውን በመለየት ማህበረሰብ አቀፍ የመረጣ (Community Based Selection) ምርምር በማድረግ ከላይ ለተጠቀሱ ችግሮች መልስ ለማግኘት ተችሏል፡፡ ለዚህም ዋና ዋና ማሳያዎቹ በሁለት አመት ሶስት ጊዜ የሚወልዱ እናት በጎች በአመት ሁለት ጊዜ መውለድ መጀመር፣ ጥሩ የኮርማነት ባህርይ (Libido) ያላቸውን አውራዎች፣ ጥሩ የእናትነት ባህርይ (Motherning ability) ያላቸውን እናት በጎችን ወዘተ... ለማግኘት ተችሏል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚያሳየው የሀገረሰብ በጎችን ለማሻሻል መረጣ ቀላል ዘዴ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም አስፈላጊውን የመረጃ ክትትል ማለትም የአንድ ግልገል የእናትና የአባት ታሪክ፣ እናት የተጠቃችበት ቀን፣ ያጠቃት አውራ፣ የውልደት ቀን፣ ፆታ፣ ቆዳ ቀለም (coat color)፣ የወሊድ ክብደት፣ የሶስት ወር ሰውነት ክብደት (ጡት ሲጥሉ የነበረው)፣ የስድስት ወርና የአመት ክብደት በመሰብሰብ ለወደፊት ጥሩ እናትና አባት ሊሆኑ የሚችሉትን ግልገሎች በመምረጥ በግ አርቢውን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡

### 5.4.1. የአባትነት ዘር ሀረግ መረጣ (paternal line Selection) ማድረግ

የተመረጠ አውራ መጠቀም የተመረጠ ግልገልን ለማግኘት ትልቅ ፋይዳ እንዳለው በመግቢያችን ላይ ለማንሳት እንደሞከርነው፤ ሁሉንም ባህርያት (traits) ያሟላውን አውራ በመምረጥ የተሻለ ግልገል በቀላሉ ማግኘት ይቻላል፡፡ ይህንን ለማሳካት ነባር የአርቢውን ዕውቀት "ከሁለት እግር ሴትን ከአራት እግር ወንድን" የሚለውን አባባልና ሳይንስን በማገናኘት ጥሩ የአውራ ባህርይ ያለውን በመምረጥ የተፈለገውን ባህርይ ማሳካት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አንድ አውራ በግ በአርሶ አደር አያያዝ በየሳምንቱ ብዙ እንስት በጎችን ቢያጠቃና ሴላው ደግሞ አንድ እናት በዓመት በአማካይ 2 ግልገሎች ከምትወልዳቸው ጋር ሲነፃፀር የሚፈለገው አላማ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ግልገሎችን ማግኘት ስለሆነ የበግ ዝርያን በመረጣ ለማሻሻል ከእንስት በግ መረጣ ይልቅ የአውራ በግ መረጣ ማካሄድ በአጭር ጊዜና ፈጣን የዝርያ መሻሻል ውጤት ያስገኛል፡፡


እንደ ቦንጋ በግ ነባራዊ ሁኔታ፣ የቦንጋ በጎች በባህሪያቸው በአጭር ጊዜ ለገበያ የሚደርሱ ከመሆናቸው አኳያ ሥራው በተጀመረ በሶስት ወር የመጀመሪያ ዙር ምርጥ የቦንጋ በግ አውራ ቅድመ መረጣ ጡት እስከሚጥሉበት ወቅት ድረስ ያለውን መረጃ መሠረት በማድረግ መረጣ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ጥሩ ታሪክ ያላቸው ግልገሎች ወደ ገበያ ወጥተው እንዳይሸጡ መከላከል ለቀጣይ ዋና መረጣ ጉልህ ፋይዳ ስላለው ነው፡፡

## የኮርማ በግ መረጣ ሂደት

- ▶ በአካባቢ የሚገኙ በግ አርቢዎች የሚፈልጉትን የአውራነት ባህርያት እንዲለዩ ማድረግ፣
- ▶ ለተለዩት ባህርያት ኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸውን መገምገምና መረጃ መሰብሰብ፣
- ▶ ለተለዩት ባህርያት አስፈላጊዉን መረጃ በመያዝ በቀጣይ የሚመጣውን ለውጥ መተንበይ (ለምሳሌ:- የክብደት ለውጥ (እድገት) ከX ወደ Y እናደርሳለን....)፣
- ▶ የአርሶ አደር የመረጣ መስፈርቶችን መለየት፣
- ▶ የእናትና የአባት ታሪክ፣ የውልደት ቀን፣ ፆታ፣ የፀጉር ቀለም (coat color)፣ ሲወለድ የነበረ ክብደት፣ የሶስት ወር (ጡት ሲጥሉ የበረው የሰውነት ክብደት) ፣ የስድስት ወርና የዓመት ክብደት መረጃዎችን መሰብሰብ፣
- ▶ የአካባቢ በጎች እድገትና የገበያ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የመረጣ ጊዜ-ሰሌዳ ማውጣት፣
- ▶ ሁሉም በአንድ ቀን ቢወለዱ በሚል እሳቤ የሁሉንም ክብደት ወደ አንድ ቀን በመለወጥ፤ ክብደታቸውን በማወዳደርና የትኛው በግ የበለጠ ክብደት አለው በማለት እንዲሁም የአርሶ አደሮችን የመረጣ መስፈርቶች ከዚህ ክብደት ጋር በማጣመር የመረጣ ሥራ መጀመር፣
- ▶ እንደ ቦንጋ በግ፤ የሚመረጡ አውራዎች የሚመረጡበት መስፈርት በመጀመሪያ የተወሰደው ታሪክና ክብደት እና በሶስተኛው ወር የተወሰደው ተጨማሪ መረጃ ማለትም የክብደት ለውጥ (እድገት)፣ ቁመት፣ አቋም፣ የቆዳ ቀለምና የላት አይነት ሆኖ ይህም የቦንጋ በግ ዝርያ ልዩ ባህርያትና የምርጫ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ለመስፈርቶቹ ኢኮኖሚያዊ ዋጋ (Economic Value) በመስጠት ነው::
- ▶ በተመረጠው አውራ ላይ አርሶ አደሮቹ ቁመናውን፣ የቆዳ ቀለሙን፣ ላቱን ወዘተ... እንዲመለከቱ በማድረግና ለዘር መሆን ያለመሆኑን እንዲያረጋግጡ ማድረግ፣
- ▶ የተመረጡትን አውራዎች በበግ አርቢ ህብረት ስራ ማህበሩ አደረጃጀት ላይ በወጣው ውል መሠረት በአባላት እጅ እንዲቆዩና ለጥቂ አገልግሎት እስኪደርሱ ድረስ በአደራ እንዲጠበቁ በማድረግ በምርጫው ወቅት ለዘር የማይሆኑትን አውራ በጎች እዛው እንዲኮላሹና አባላቱ እንዲያሞክቱ ማድረግ::

- ▶ የመረጣው ዙር እንደ ዝርያና አካባቢው ሁኔታ የሚወሰን ሲሆን እንደ ቦንጋ በግ ነባራዊ ሁኔታ የሚመረጡ አውራዎች መጀመሪያ ከተወሰደላቸው ታሪክና ክብደት እና በሶስተኛ ወር በተወሰደላቸው ተጨማሪ መረጃዎች ማለትም የክብደት ለውጥ (እድገት)፣ ቁመት፣ አቋም፣ የቆዳ ቀለምና የላት ዓይነትና ቀንድ አልባ ሆኖ ይህም የቦንጋ በግ ዝርያ ልዩ ባህርያትና የምርጫ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ቅድመ ምርጫ (pre-selection) አውራው ከተወለደበት በሶስት ወርና የመጨረሻ (Final selection) በስድስት ወር በማድረግ እንዲሁም ማንኛውንም አካላዊ እንከኖችን በማየትና በመለየት ከሶስት እስከ አራት ዙር መረጣ ማድረግ ይቻላል::

- የተመረጡ አውራዎችን በተሻሻለ መኖ፣ ጤናና ቤት አያያዝ መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡
- አንድ አውራ ከ25-30 እንስት በጎች ጥቂ እንዲውል በሚል ስሌት የቀሩትን ወደ ሌላ አካባቢ ስርጭት ማድረግ፡፡
- በተመረጡ አውራዎች የተወለዱ ግልገሎችን ግምገማ በማድረግ ጥሩ የአባትነት ዘር ሀረግ ያለውን የዘር መስመር (Line) በመከተል የቀጣይ ምርጫ ማድረግ፡፡
- በማህበር አባላት መንደር (Community) ላይ የሚያጠቁ አውራዎች ከአጠቃላይ አውራዎች ውስጥ ምርጥ አስሮቹ መሆን አለባቸው፡፡




ምስል 2.1. የቦንጋ በግ ኮርማ መረጣ ተግባራት

## በመረጣ የተሻሻለ የቦንጋ አውራ በግ መለያ ባህርያትና ዕ[illegible]ታዎች

- ✓ **ቀለሙ** - ጥቁር አይደለም፤ አብዛኛውን ጊዜ ቀይ፣ ቀይ መጋላና ዳለቻ ነውለ፡፡ ሌሎች የቆዳ ቀለሞችም ሊኖረው ይችላል፡፡
- ✓ **ቀንድ** - የለውም፡፡
- ✓ **አካላዊ ገፅታው** - በጣም ጎልቶና ወጣ ብሎ የሚታይ ፍርምባና ጋማ መሰል ፀጉር ማጅራቱ ላይ ያለው ነው፡፡ ትልቅና ረጅም ወይም የተጠንለጠለ ላት ያለው፣ አፍንጫውናና ጭንቅላቱ በጣም ትልቅ የሆነ እና ከፊትም ሆነ ከኋላ ሲታይ የአንበሳ አቋም ያለው ነው፡፡
- ✓ **የጥቂ ፍላጎቱ** - የጥቂ ፍላጎት ባህርይው (Libido) በጣም ከፍተኛ የሆነና
- ✓ **ክብደቱ** - የአመት ክብደቱ እስከ 60 ኪ.ግ የመመዘን አቅም ያለው ነው፡፡



ምስል 2.2. የቦንጋ አውራ በግ መለያ ባህርያት

## 5.4.2. የእናትነት ዘር ሀረግ መረጣ (maternal line Selection) ማድረግ

ምንም እንኳን "ከሁለት እግር ሴትን ከአራት እግር ወንድን" የሚል የአካባቢያዊ አይታዎች ቢኖሩም ከተመረጡ ወንድና ሴት የምርጦቹ ምርጥ ግልገልን ማግኘት ይቻላል:: ምክንያቱም ሁለቱም ቤተሰቦቹ ምርጥ ከሆኑ ወደ አንድ ግልገል የሁለቱም ቤተሰብ በራሂ (Gene) ውህደት (50:50) ስለሚተላለፍ ነው:: ስለሆነም ልክ እንደ አውራዎቹ ያጥሩ እናትነት ባህርያት ያላቸውን እናት በጎች በመለየትና መረጣ በማድረግ የሆገረሰብ በግ ዝርያን ማሻሻል ይቻላል::


## የመረጣ ሂደት


- በአካባቢ የሚገኙ በግ አርቢዎች የሚፈልጉትን የእናትነት ባህርያት እንዲለዩ ማድረግ፣
- ለተለዩት ባህርያት ኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸውን መገምገምና መረጃ መሰብሰብ፣
- ለተለዩት ባህርያት አስፈላጊዉን መረጃ በመያዝ ቀጣይ የሚመጣውን ለውጥ መተንበይ (ለምሳሌ:-ግልገሎችን የማሳደግ አቅም፣ መንታ የመወለድ ወዘተ...)፣
- የአርሶ አደር የመረጣ መስፈርቶችን (preferred traits) መለየት፣
- የእናቲቷን ታሪክና ሌሎች መረጃዎችን መሰብሰብ፣
- የአካባቢ በጎች እድገትና የገበያ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የመረጣ ጊዜ-ሰሌዳ ማውጣት፣
- ሁሉም በአንድ ቀን ቢወልዱ በሚል እሳቤና ከወለዱትም ማን ቶሎ አሳደገ፣ የማን ግልገል ጥሩ ክብደት (weaninge weight) መዘነ ወዘተ... ወይም የሚመረጡት ቄቦች ከሆኑ የእናታቸውና የአባታቸውን ታሪክ የአርሶ አደር የመረጣ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የመረጣ ሥራ መጀመር፣
- የተመረጡ እንስቶችን የማህበር አባላት ወደ ገበያ ሳያወጡ እንዲጠብቁና በምርጫው ወቅት ለዘር የማይሆኑ እናቶችን በማውጣት በተሻለ እንዲተኩ ማድረግ፣
- የተመረጡ እንስት በጎችን በተሻሻለ መኖ፣ ጤናና ቤት አያያዝ በመንካባከብ በተመረጠ አውራ ብቻ እንዲቁ ማድረግ፣
- ከተመረጡ እንስት የተወለዱ ግልገሎችን ግምገማ በማድረግ ጥሩ የአባትነትና የእናትነት ዘር ሀረግ ያለውን (Line) በመከተል የቀጣይ ምርጫ ማድረግ፣
- ቀጣይ በማህበረሰቡ (Community) ዉስጥ የሚጠቁ እንስቶች ከምርጦቹ አውራዎች ብቻ መሆን አለባቸዉ::

## በመረጣ የተሻሻሉ የቦንጋ እናት በግ መለያ ባህርያትና እይታዎች

- ✓ መንታ፣ ሶስትና አልፎ አልፎ አራት የመውለድ ባህርይ፣
- ✓ የተወለዱ ግልገሎችን የማሳደግ የእናትነታቸው ባህርይ ብቃት ከፍተኛ የሆነ፣
- ✓ ትልቅና ለአካላዊ እይታ የሚመቹና
- ✓ ቶሎ ለመጠቃት የሚደርሱ ናቸዉ::

ምስል 2.3. በመረጣ የተሸሻሉ የቦንጋ እናት በጎች








ምስል 2.4. በመረጣ የተሻሻሉ የቦንጋ እናት በጎችና ግልገሎች

# 6. ሥነ-ምግብና እና የአመጋገብ ጥንቅር

የቦንጋ በጎች ዋነኛው የመኖ ምንጭ የተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ሲሆን አርሶ አደሮች መጠኑ ብዙ ባይሆንም የቤት ጥራጊን (ማለትም ከሰዉ ማእድ የተረፈዉን ምግብ፣ የቡና አተላ፣ የአረቂ አተላ፣ የጠላ አተላና የመሰሰሉትን) አዘዉትሮ የመመገብ ልምድ አላቸዉ። አሁን አሁን የተሻሻሉ የመኖ ዝርያዎችን በተለይም የደሾ ሣርን በበጋ ጊዜ ይበልጥም ለም (አረንጓዴ) የግጦሽ ሣር እንደ ዝናባማ ወቅት በማይገኝበት ጊዜ መጠቀም በስፋት እየተለመደ መጥቷል።

## 6.1. ከእርባታ አገልግሎት የተወገዱ በጎችን ማሞከት

### 6.1.1. የሚሞከቱ በጎች አመራረጥ

የቦንጋ በጎች እድገት ፈጣን መሆኑና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለእርድ ስለሚደርሱ ለማሞከት ሥራ የሚመረጡ በጎች ከዝርያ ማሻሻያ መረጣ የተወገዱ ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት የሆኑ በጎች መሆን አለባቸዉ። የበጎቹን ዕድሜ ጥርሳቸዉን በመመልከት መገመት ይቻላል። የሚሞከቱ በጎች በአቋማቸዉ (frame) የተሻለ ቁመትና ርዝመት ኖሮአቸዉ በቂ ስጋ የመሸከም አቅም እንዲኖራቸው አጥንተ-ሰፋፊ መሆን ይገባቸዋል።

በእንስሳት ጤና ባለሙያ በመታገዝ የበጉን እንቅስቃሴና ንቃት በማየት በዓይን የሚታይ የጤና ችግር የሌለበት መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነዉ። ለማሞከት ሥራ በጎቹ ከተለዩ በኃላ በጤና ባለሙያዎች ድጋፍ:-

- በአካባቢዉ በተደጋጋሚ ለሚከሰቱ በሽታዎች ክትባት መስጠት፣
- ለዉስጥና ለዉጭ ጥገኛ መድኃኒት መስጠት እና
- በጎቹ ሞክተዉ እስከሚወጡ ድረስ ለሚከሰቱ የጤና ችግሮች ህክምና እንደ አስፈላጊነቱ መስጠት ያስፈልጋል።

## 6.1.2. የመኖ አይነቶችና አዘገጃጀት

መኖ ለማሞከት ሥራ ከሚያስፈልገዉ ወጪ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ የማሞከት ሥራን ዉጤታማ ለማድረግ የሚዘጋጀዉ መኖ ሥራዉ በሚካሄድበት አካባቢ በስፋት የሚገኝና ርካሽ መሆን ይኖርበታል::

አብዛኛው የመኖ ምርምሮች በሂደት ላይ ቢሆኑም በአርሶ አደር አያያዝ በቀን ለአንድ በግ እንደየ ሰዉነት ክብደት መጠን ከ1-2 ሌትር የአረቄ አተላ 500-600 ግራም ከተሸረከተ በቆሎና ስንዴ ጋር የግጦሽ ሣርን ከመደበኛ መኖአቸዉ ጋር አቀላቅሎ በመመገብ ለ3 ወር በተጠና ሙከራ በቀን በአማከይ 102 ግራም ክብደት እንደሚጨምሩና ከ500-800 ብር ከአንድ በግ የተጣራ ትርፍ እንደሚገኝ ለማየት ተችሏል:: ዉሃ ለማሞከት በጣም አስፈላጊ ስለሆነ በየቀኑ በቂና ንጹህ ዉሃ በዉሃ መጠጫ ገንዳ መሰጠት አለበት:: በመሆኑም የዚህን ምርምር ሙከራን የአርሶ አደሩን የገቢ መጠን ለመጨመር፣ ወጣቶችንና ሴቶችን በማደራጀትም ሆነ በ"Investment" ለሚሳተፉ ባለሀብቶች አዋጭ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል::

በተጨማሪም የቦንጋ በግ በባህይው ለም (አረንጓዴ) ሳሮችን የሚፈልግ ከመሆኑ አንፃር የተሻሻለ የመኖ ዝርያ (የደሾ ሣር) አርሶ አደር በየማሳው በሦስት አንጓ ርዝመት (25 ሴ.ሜ) እየቆረጡ በዘር መሀል 0.75 ሜትር፣ በመስመር መሀል 0.5 ሜትር ርቀት እንዲተክሉና ለም (አረንጓዴ) ሳር እጥረት ባለበት ወቅት አጭደው እንዲመግቡ በማድረግ የመኖ እጥረትን ለማካካስ ተችሏል:: ስለሆነም በዚህ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ግለሰቦች እንደ ሁኔታዉ በሚኖራቸዉ የመኖ ማልሚያ መሬት ላይ ማምረት ይቻላል::

## 6.1.2. የመኖ አመጋገብ ስልት

አበዛኛዉን ጊዜ ለተመጣጠነ መኖ አዲስ ስለሚሆኑ መጠኑ ቀስ በቀስ እየጨመረ እንዲሄድ በማድረግ እንዲለምዱት ማድረግ ይገባል:: የመመገቢያ ገንዳ ከ2-4 ሜትር ርዝመት ያለዉ ከአካባቢ በሚገኝ ቁሳቁስ የተሠራ የመመገቢያ ገንዳ በማዘጋጀት የሚሞከቱ በጎችን መመገብ ያስፈልጋል::

### 6.1.3. የማሞከቻ ወቅት

የገበያ ሁኔታንና የመኖ አቅርቦትን አስተማማኝ በማድረግ በአንድ አመት 3 ዙር ማድለብ ይቻላል:: በአንድ የማሞከቻ ጊዜ እስከከ 90 ቀናት ባለዉ ጊዜ አሞክቶ ለገበያ የሚያቀርብበት ስልት መነደፍ ይኖርበታል:: የማሞከት መርሀ-ግብሩን ከህዝብ በዓላት (ዘመን መለወጫ፤ ፋሲካ፤ ገና ወዘተ…) ጋር በማያያዝ የተሻለ ገበያ እና አመርቂ ዉጤት እንዲያስገኝ ማድረግ ይቻላል:: ስለዚህ ለማሞከት በሚወሰንበት ጊዜ በየትኛዉ በዓል በጎቹ እንደሚሸጡ በቅድሚያ የጊዜ ሰሌዳ መዘጋጀት ይኖርበታል::



ምስል 2.5. በአረቄ አተላ፣ ከተሸረከተ በቆሎና ሰንጴ በ3 ወር ውስጥ የተደለበ በግ

## 7. የጤና ጥንቅር

### 7.1. በሽታዎችና የመከላከያ ዘዴዎች

የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሌላው መሰረታዊ ነገር የጤና አጠባበቅን ማጠናከር ነው፡፡ እንደ ቦንጋ በጎች ነባራዊ ሁኔታ ያሉትን በሽታዎች ለመለየት ቀጣይ ጥናቶች የሚያስፈልግ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ባለው ጥናት መረጃ መሰረት፡-

1. የበጎች ጎሮሮሳ በሽታ (Ovine pastureollosis) በደማቸው እንደሚገኝ፣

2. ደስታ መሰል የበጎችና ፍየሎች በሽታ (PPR) እንደማይገኝ፣

3. የውስጥና የውጭ ጥገኛ ተዋህስያን (መዥገር እና ቅማል) እንደሚገኙ ለማረጋገጥ ተችሏል:: በዚሁ መሠረት ስትራቴጂክ (Strategic) የሆነ የጤና ቅድመ-መከላከልና አጠባበቅ ስራዎችን መተግበር ያስፈልጋል:: **ስለሆነም:-**

1. ዝናብ በሚጀምርበት (ከመጋቢት-ሚያዝያ) እና ዝናብ በሚያቆምበት (ከመስከረም-ጥቅምት) ወቅት የበጎች ኀሮሮሳ በሽታ (Ovine pastureollosis) ክትባት በመስጠት በሽታን መከላከል ይቻላል::

2. የውስጥ ጥገኛን ለመከላከልም ሆነ ለማጥፋት በአመት (በየሶስት ወሩ) የውስጥገኛ መከላከያ መድኃኒቶች (Deworming with Albendazole 300mg, 600mg & Ivermectin) መሰጠት ይኖርበታል::

3. የውጭ ተዋህስያንን በአመት ሁለት ጊዜ በሚከሰትበት ወቅት አስፈላጊውን ክትትል (ለምሳሌ acaricides በመጠቀም) መካላከል ይቻላል:: በቦንጋ በግ ላይ ከዝርያ ማሻሻያ ፕሮግራም ጋር ተያይዞ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን የጤና አጠባበቅ ስልቶችን በመቀየስ የግልገሎች፣ አውራዎችና እናቶችን ሞት (mortality) በመቀነስ የዝርያ ማሻሻያ ስራን ለማሳካት ተችሏል::

**8. የቦንጋ በግ ዝርያን ለማሻሻል በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰራ ሥራና የተገኘ ውጤት**

የቦንጋን በግ ዝርያ በማህበረሰብ ተሳትፎ የመምረጥና የማሻሻል ስራ በካፋ ዞን በአዲዮ ወረዳ በቦቃ ቀበሌ በILRI-ICARDA_BOKU ፕሮጀክትና በቦንጋ ግብርና ምርምር ማዕከል በተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት መሠረት የቦንጋ የበግ ዝርያ በሀገራችን ከሚገኙ የሆሮ፣ የመንዝና የአፋር የበግ ዝርያዎች የተሻለ የአንድ አመት እድሜ ክብደት፣ የእናት በጎች ክብደት፣ የተሻለ መንታ የመውለድ ባህርይና እንዲሁም የተሻለ ወልዶ የማሳደግ ባህርይ እንዳለው አረጋግጧል:: በተጨማሪም የቦንጋ በግ ዝርያ ወንዶች:-

- ከአፋር ተመሳሳይ እደሜ በጎች በ13 ኪ.ግ፣
- ከሆሮ በጎች በ3 ኪ.ግ እና
- ከመንዝ በጎች በ12 ኪ.ግ የሚበልጡ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል::

ከእነዚህ በተጨማሪ ለርቢ የደረሱ የቦንጋ በግ ቄቦችም

- ከአፋር በጎች በ11 ኪ.ግ ፣
- ከሆሮ በጎች በ3 ኪ.ግ እና
- ከመንዝ በጎች በ10 ኪ.ግ የሚበልጡ መሆናቸውን በጥናቱ ተረጋግጧል::

በዚሁ በቦቃ ቀበሌ በተካሄደው የበግ አውራዎች መረጣና በእነዚሁ በተመረጡ አውራዎች ማዳቀል በመጀመሪያው ትውልድ ብቻ የግልገሎችን የወሊድ ክብደት ከ2.5 ወደ 5.8 ኪ.ግ ከፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በ3 ወር እድሜአቸው እስከ 29 ኪ.ግ ክብደት ያላቸው በጎችን ማግኘት መቻሉ የተመረጠ አውራ መጠቀም የተመረጠ ግልገልን ለማግኘት ያለውን ፋይዳ በግልጽ ያሳያል:: ከዚህ ስራ ጋር ተያይዞ በክልላችንም ሆነ

በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ የሆነ የበግን ዝርያ በመረጣ የሚያሻሽል የአርሶ አደሮች የህብረት ስራ ማህበር በካፋ ዞን ቦቃ ቀበሌ በማቋቋም አርቢዎች ከዝርያ ማሻሻያ ጎን ለጎን አውራዎችን እያባዙ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች እንዲያሰራጩ ተደርጓል፡፡ የዚህ ዓይነትን ምርጥ ተሞክሮ ለሁሉም አርሶ አደሮች ማስፋት ከተቻለ ከቦንጋ የበግ ዝርያ ?ሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር ገበያ የሚፈልገውን የእድሜና የስጋ ክብደት ደረጃ በተፈለጊው ጊዜ ሊያሟሉ የሚችሉ በጎችን በማግኘት የአርቢውን ህብረተሰብ ገቢና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 9. የቦንጋ በግ የርቢ ባህሪያት


የቦንጋ በግ የመዉለድ አቅሙ (litter size) 1.37 ሲሆን ከመቶ (100) እናት በጎች በአማካይ በአንድ ወሊድ 137 ግልገሎችን ማግኘት እንደሚቻል ሲያመለክት መንታ (50.87%)፣ አንድ (46.92%) እና ሶስት (2.21%) የመውለድ አቅማቸው ከፍተኛ ሲሆን የበጉ መንጋ ሁኔታን በሚመለከት የአንድ ሰው አማካይ ይዞታም 8.5 እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ የቦንጋ በግ ዝርያ ማሻሻያ ፕሮግራም ከመጀመሩ በፊት በተደረገዉ ጥናት አንዲት ቄብ የመጀመሪያ ግልገሏን የምትወልደው በ14.92 ወር ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በጥሩ እንክብካቤ ያደገች አንዲት ቄብ በግ በተወለደች በ14.6 ወሯ መዉለድ የምትችል መሆኑን በቅርቡ የተደረገ ጥናት ያሳያል፡፡ ከአንደኛዉ ወሊድ እስከ ቀጣዩ ወሊድ 8.9 ወር ከነበረው ወደ 8.5 ወር (255 ቀናት) በአማካይ መቀነስም ተችሏል፡፡ አንዲት የቦንጋ እናት በግ ግልገል እንደወለደች (PPW) በአማካይ 34.3 ኪ.ግ ስትመዝን አንድ የቦንጋ ግልገል በተወለደ በ6 ወሩ ትክክለኛ ጥቂ እንደሚጀምር ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

## 9.1. የቦንጋ በግ የዕድገት ባህርያት


ቀደም ሲል በተደረገ ጥናት የቦንጋ በግ በወሊድ 2.7 ኪ.ግ የሚመዝን ሲሆን የዝርያ ማሻሻያ ሥራ ከተጀመረ ወዲህ ግን የቦንጋ በግ የወሊድ ክብደት በአማካይ 5.8 ኪ.ግ እንደደረሰ በቅርብ የተደረገ ጥናት አመልክቷል፡፡ አማካይ የጡት መጣያ እና የስድስት ወር ክብደቱም እንደየ ቅደም ተከተላቸው 15.5 እና 22.2 ኪ.ግ እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ የቦንጋ ግልገሎች ከወሊድ እስከ ሶስት ወር ዕድሜ (ጡት መጣያ) ድረስ በቀን በአማካይ 129.1 ግራም የሚጨምሩ ሲሆን ከጡት መጣያ እስከ 6 ወር ዕድሜ ደግሞ በቀን 69.3 ግራም በአማካይ ይጨምራሉ/ ያድጋሉ፡፡ ይህም የቦንጋ በግን በሀገራችንም ሆነ በክልላችን በፈጣን ዕድገት ግንባር ቀደም ያደርገዋል፡፡

## 10. የቦንጋ በግ ዝርያ ስርጭት

የቦንጋ በግ ዝርያ ባሉት ልዩ ባህርያት እና ቶሎ የማደግና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለእርድ የመድረስና በሀገሪቱ ካሉት በጎች ውስጥ በትልቅነቱ ቀዳሚ ከመሆኑ አንፃር 1,425 በመረጣ የተሻሻሉ የቦንጋ አውራዎች ወደ ተለያዩ የሀገሪችን ክፍሎች ተሰራጭተዋል:: በአጭር ጊዜ ውስጥ ብቻ በሁሉም የደቡብ ክልል ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች፣ በኦሮሚያ ክልል አምቦና ሆሮ ጉድሩ፣ትግራይ ክልል አላማጣ አካባቢዎች እና በአዲስ አበባና ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲዎች የተሰራጩ ሲሆን በተሰራጩበት አካባቢ፤ አካባቢውን የመልመድ፣ ከአካባቢ በጎች ጋር በመዳቀል መንታና ሶስት የመውለድ አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን ግብረ መልሶች በግልፅ ያመላክታሉ::




ግራፍ 2.1. በአርሶ አደር ተሳትፎ በተከናወነ መረጣ ተመርጠው የተሰራጩ የቦንጋ በጎች




ግራፍ 22. ማኅበረሰብ አቀፍ የቦንጋ በግ ዝርያ ማሻሻል ሥራ ኢኮኖሚን ለማሳደግ ያበረከተው አወንታዊ ተፅዕኖ

## 11. የፓኬጁ ስርጭት ስልት / አተገባበር ቅድመ ሁኔታዎች

የሀገረሰብ በግ ዝርያ ማሻሻያ ፓኬጅ ከላይ የተጠቀሱ ስልቶችን በመጠቀም ወደ ተጠቃሚው የሕብረተሰብ ክፍል የሚከተሉትን ዋና ዋና ስልቶች በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል::

### 11.1 ሥልጠና መስጠት

የፓኬጁ ዓላማና የሚያስገኘው ጥቅምን በሚመለከትና እንዲሁም ፓኬጁን በታቀደለት መሠረት ግብ እንዲመታ ለማድረግ የሚጠይቀውን የቴክኒክ ዕውቀት ለማስጨበጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

ሀ. የባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ፣

ለ. የባለሙያዎች ሥልጠና፣

ሐ. የአርሶ አደሮች (የበግ አርቢዎች) ሥልጠና /መድረክ/::

ከየወረዳው የተወጣጡ ባለድርሻ አካለት ማለትም የእንስሳት ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የግብይትና ሕብረት ስራ ኃላፊ፣ የወረዳ አስተዳዳሪ እና በተመሳሳይ መልኩ በዞን ደራጃ ያሉ ኃላፊዎች በአካባቢው በሚገኝ ምርምር ማዕከል አማካኝነት ተገቢውን ሥልጠና ሰጥቶ እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ እስከ ቀበሌ የሚወርድ አነቃቂ ሰነዶችንና መፈክሮችን ማዘጋጀት:: እንደ አካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ሰነዶች ከተዘጋጁ በኃላ ለወረዳና ለቀበሌ እንስሳት እርባታ ባለሙያዎችና አደራጅ ባለሙያዎች ስለ ሀገረሰብ በግ ዝርያ ማሻሻያ ፕሮግራምና በተገኙ ተሞክሮዎች ላይ ሰፊ ስልጠና በመስጠት የተዘጋጀውን ሰነድ ወደ ታች በማዉረድ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ:: እነዚህ ሰልጣኞች ደግሞ ወደ ታች በመውረድ ለበግ አርቢው ሰፊ ህብረተሰብ ግንዛቤ በመስጠትና አንዳንድ የዝርያ ማሻሻያ ስራን የሚያነሳሱ መፈክሮችን በማዘጋጀትና ለበግ አርቢው ህብረተሰብ ሰፊ ገለፃ በማድረግ እንዲሁም የስልጠና መድረኮችን በማዘጋጀት ስልጠና መስጠት የስፈልጋል:: ለዚህ አላማ መሳካት ምቹ አጋጣሚዎችን መጠቀም ለምሳሌ የልማት ቡድን አደረጃጀቶችን መጠቀም ይቻላል::

### 11.2. ልምድ ልውውጥ ማድረግ

በወረዳ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ቀበሌያት ላይ በአንድ ጊዜ የማህበረሰብ አቀፍ የበግ ዝርያ ማሻሻያ ፕሮግራም ከመስራት ይልቅ የተወሰኑ ሞዴል ቀበሌያትን ብቻ በመምረጥ የሚታይ ስራ በመስራትና በፕሮግራሙ ባልታቀፉ ቀበሌያት የሚኖሩ ሞዴል አርሶ አደሮችን በመምረጥ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ በማድረግ ስለ ሀገረሰብ በግ ዝርያ በመረጣ የማሻሻል ስራን የመቀበል ፍላጎታቸውና ተነሳሽነታቸው እንዲጠናከር መደረግ አለበት:: በተጨማሪም እነዚህ ሞደል አርሶ አደሮች በአካባቢያቸው ያሉትን መሰል አርሶ አደሮች በተዋረድ እንዲያስተምሩ በማድረግ የማህበረሰብ አቀፍ የበግ ዝርያ ማሻሻያ ፕግራም ማስፋት ሂደቱን እንዲፋጠን ያደርገዋል::



ምስል 2.6. የቦንጋ የበግ ዝርያ የማስተዋወቅ ሥራዎች

## 11.3. የብዙኃን መገናኛ አካላትን በመጠቀም ፓኬጁን ማስተዋወቅ

የእንስሳት ምርት እንዳያድግ ከሚያደርጉት ማነቆዎች ዋና ዋናዎቹ በሕብረተሰቡ ዘንድ ያለው በመረጣ ላይ የተመሰረተ ዝርያ ማሻሻያ ላይ ያለው ዝቅተኛ አመለካከት እና የገበያ ችግር ቢሆንም በአሁኑ ወቅት እነዚህ ችግሮች ሙሉ በሙሉ ባይቀረፉም መንግስት በሰጠው ልዩ ትኩረት በርካታ መሻሻሎች እየተመዘገቡ ናቸው:: በእንስሳት ዝርያ ማሻሻያና በተጓዳኝ የሚሰሩ ስራዎችን ገበያው በሚፈልገው መሠረት በማምረት እና ከተጠቃሚው ጋር ለማስተሳሰር የገበያ መሠረተ ልማቶችን በማጠናከር የገበያ ችግርም ሆነ ሌሎችን ችግሮች በቀላሉ መፍታት ይቻላል::

ማህበረሰብ አቀፍ የሀገረሰብ በግ ዝርያን በመረጣ ማሻሻል ዘዴ አዋጭነቱን ለተጠቃሚው (ለበግ አርቢው) በማድረስ ረገድ የመገናኛ ብዙሃን ትልቅ ሚና ይጫወታሉ:: ስለዚህ የሀገረሰብ በግ ዝርያን ገበያው በሚፈልገው መሠረት በማምረት ለሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ላለ ገበያ በማረብ ምንዛሪን ከማሳደግ ባለፈ ዝርያው እንዳይጠፋና እንዳይመናመን ማህበረሰብ አቀፍ የሀገረሰብ በግ ዝርያን በመረጣ የማሻሻል ዘዴ ጥሩ አማራጭ እንደሆነ የመገናኛ ብዙሃን (የካከባቢ ሬዲዮ ጣቢያዎችን) እና የማስታወቂያ ስልትን በመጠቀም በተደጋጋሚና በተከታታይ ረዘም ላለ ጊዜ ማስተዋወቅ ተገቢ ይሆናል::

## 11.3. የብድር አገልግሎት ማቅረብ

በመረጣ የሀገረሰብ ዝርያን ማሻሻል ከብዙ ገንዘብ ይልቅ ትንሽ ጊዜ የሚፈልግ ቢሆንም የሚሰማሩ የዝርያ ማሻሻያ ማህበራትም ሆኑ ሌሎችን ከብድርና ቁጠባ ተቋማት ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል:: ስለዚህ ብደሩን የሚያቀርቡትት የገጠር የብድር አገልግሎት ተቋማት ትልቅ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል::

## 11.4. የሚያስፈልጉ ግብአቶች

ለዝርያ ማሻሻያ የሚያስፈልጉ የመኖና የጤና ጥንቅሮችን እንደ ቦንጋ ነባራዊ ሁኔታ ለማሳየት የተሞከረ ቢሆንም አንዳንድ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል::

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | የአንዱ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | የጆሮ መለያ ቁ/መ /ear tag | ቁጥር | 6.5 |
| 2 | ማርከር/Ardes france/ | ፓኬት | 175 |
| 3 | Ear tag Appllicator | ቁጥር | 650 |
| 4 | ተንጠልጣይ ሚዛን (50kg) | » | 600 |
| 5 | ማኮላሻ/ቡርዲዞ/መካከለኛ | » | 670 |
| 6 | ትልቁ መዝገብ | ቁጥር | 90 |
| 7 | መካከለኛ መዝገብ | » | 60 |
| 8 | ደብተር ባለ 32 ገጽ | » | 3 |

ሰንጠረዥ 2.1. ለዝርያ ማሻሻል የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በመጠንና በዋጋ

# 12. የፓኬጁ ታሳቢዎች

### 12.1. የመረጃ አያያዝ

የሚከተሉት መረጃዎች በጥንቃቄና በተሟላ መልኩ መያዝና መደራጀት አለባቸው::

**ሥራ ከመጀመር በፊት**

በአካባቢ የሚገኙ በጎች የአወላለድ ታሪክ፣ የእድገት ደረጃዎችን (የወሊድ፣ የ3 እና የ6 ወርና የአመት ክብደት ወዘተ...) ለይቶ በመያዝ ቀጣይ ከሚመጣው የክብደት ለውጥ ጋር ማወዳደር ያስፈልጋል:: በተጨማሪ የአርሶ አደሩ ግንዛቤና የተሳትፎን ቁጥር ጭምር ለይቶ መያዝ የተሻለ ይሆናል:: በተጨማሪም ለማሻሻል የሚፈለጉ ባህርያትን አወዳድሮ በግልፅ ደረጃ በማውጣት መዝግቦ ማስቀመጥ የስፈልጋል::

**ሥራ ከተጀመረ በኋላ**

ሥራ ከመጀመር በፊት የነበረውን መረጃ ስራ ከተጀመረ በኋላ ጋር በማወዳደር የመጡ ለውጦችን በግልፅ አደራጅቶ ማስቀመጥና የመጡ ለውጦችን መለየት ያስፈልጋል:: በተጓዳኝ የሚሰበሰቡ መረጃዎች እነዚህ ብቻ ባይሆኑም ያልተቋረጠ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተጠቃሚውን ሕብረተሰብ ማብቃት ወሳኝና ትልቁ ተግባር ይሆናል::

**የቦንጋ በግ ዝርያ ባለቤትነት**

ሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ ሀገር በቀል የሆኑ የሰብልም ሆነ የእንስሳት ዝርያዎች መገኛ ምንጭ ብትሆንም እንኳ ለምሳሌ ከዳልጋ ከብት ዝርያ ቦረና እና ከሰብል ዓይነቶች የጤፍና ቡና ዝርያዎቹ ባለቤትነት የማይመለታቸዉ የዉጭ ሀገራት የራሳችን ሀገር ዝርያዎች ናቸዉ በሚል ሁኔታ ለማስመዝገብ እየሞከሩ ስለሆነ፣ መሰል የቴክኖሎጂ ስርቆት ድርጊት በዚህኛዉም በቦንጋ በግ ዝርያና በሌሎች እንስሳትና ሰብሎች ዳግም ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዳይከናወን በክልላችንም ሆነ በሀገራችን ደረጃ አስፈላጊውን ግንዛቤ ለሚመለከታቸዉ አካላት ሁሉ መስጠት ያስፈልጋል::